# በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

## የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

## የ2014 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት

## የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

**ጥር 2014 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የከተማ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# የ2014 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የ.ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 55 እና በም/ቤት አሰራርና የአባላት ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 መሰረት በህግ ተለይተው ከተሰጡት ዋና ዋና ተልዕኮዎች መካከል ህግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ አካላትን የመከታተል፣ የመቆጣጠር፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ እና የህዝብ ውክልና ስራ መሆኑ ይታወቃል።

የቋሚ ኮሚቴው አደረጃጀትና ተግባር ለመወሰን የፀደቀው ውሳኔ ቁጥር 03/2014 ዓ.ም መሰረት የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ጭምር በጠቅላላው 13 አባላት ያሉት አደረጃጀት ነው።

በመሆኑም ቋሚ ኮሚቴው የ2014 ዓ.ም የም/ቤቱ ዕቅድ እንደ መነሻ ሁኔታዎች በመውሰድ ህግ ማውጣት፣ ክትትል ቁጥጥርና የህዝብ ውክልና ስራ በመስራት የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የከተማ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ **የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት** በሚከተለው መልክ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

## የቋሚ ኮሚቴው የትኩረት መስኮች

- ትኩረት መስክ 1፡- ክትትልና ቁጥጥር
- ትኩረት መስክ 2፡- ህግ ማውጣት
- ትኩረት መስክ 3፡- የህዝብ ውክልና ስራዎች

## የዓመቱ ዕቅድ አበይት ተግባራትና ግቦች

- **የዝግጅት ምዕራፍ** ተግባራት በቋሚ ኮሚቴውም ሆነ በተጠሪ ተቋማት ደረጃ በተሟላና ብቃት ባለው ሁኔታ መፈፀም፣
- **የተግባር ምዕራፍ** ተግባራት ውጤታማ በሆነ መልኩ የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ ስራዎችን ማዕከል ባደረገ ሁኔታ መፈፀም፣

- **የማጠቃለያ ምዕራፍ** ተግባራት ለቀጣዩ የበጀት ዓመት ተገቢውን ልምድ የተገኘበትና በዓመቱ ውስጥ በነበረው ተልዕኮ ቋሚ ኮሚቴውና ተጠሪ ተቋማት በአስተዋፅኦቸው ልክ ተመዝነው መፈፀም፣

## 2. የሰው ሃብት ልማትና አቅም ግንባታ ዘርፍ ተግባራትን በተመለከተ

### የተከናወኑ ተግባራት፦

- ቋሚ ኮሚቴው ክትትልና ቁጥጥር ከሚያደርጋቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ውስጥ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ባዘጋጀው መድረክ ላይ በሚሰራቸው ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች፣ ስትራቴጂክ ዕቅዶች እና ተግባራቶቻቸውን አስመልክቶ የቋሚ ኮሚቴው ሁሉም አባላት፣ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ከተጠሪ ተቋማት በመገኘት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ 13 አባላት እና 6 ባለሙያዎች በድምሩ 19 ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።
- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ባዘጋጀው መድረክ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅድ ላይ ለቋሚ ኮሚቴ አባላት ስልጠና ሰጥቷል።
- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ባዘጋጀው መድረክ በፕላንና በጀት ልማት ሚኒስቴር የሀገሪቱ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል።
- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ባዘጋጀው መድረክ የክትትልና ቁጥጥር ማኑዋል ላይ ለአባላት ስልጠና ተሰጥቷል።
- ቋሚ ኮሚቴው ክትትልና ቁጥጥር ከሚያደርጋቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ውስጥ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ባዘጋጀው መድረክ ላይ በሚሰራቸው በፖሊሲዎች፣ በስትራቴጂዎች፣ በሴክተሩ ፒላሮችና ትኩረት መስኮች፣ በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች እንዲሁም በረጅም ጊዜ ዕቅድ አስመልክቶ የቋሚ ኮሚቴው ሁሉም አባላት፣ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ከተጠሪ ተቋማት በመገኘት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ 10 አባላት እና 6 ባለሙያዎች በድምሩ 16 ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

**የተገኘ ውጤት፦** በተሳተፍንባቸው መድረኮች ላይ የተለያዩ ግንዛቤዎችን ለማግኘት ተችሏል።

## 3. የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ

**የተከናወኑ ተግባራት፦**

- የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅትን አስመልክቶ ተገምግሞ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ ግብረ-መልሱ ተልኳል።
- ቋሚ ኮሚቴው ክትትል ከሚያደርጋቸው ተቋማት መካከል የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት አንዱ ሲሆን በዘርፉ ከሚሰሩ ፕሮጀክቶች መካከል የፌደራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚያስገነባቸው የመንግስት ህንፃ ግንባታ ላይ የከተማ መደበኛ መስክ ምልከታ ተከናውኗል።
- ቋሚ ኮሚቴው ክትትል ከሚያደርጋቸው ተቋማት መካከል የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት አንዱ ሲሆን ዘርፉ ከሚሰጠው አገልግሎት ውስጥ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት ድንገተኛ ምልከታ ተከናውኗል።
- ቋሚ ኮሚቴው ክትትል ከሚያደርጋቸው ተቋማት የሁለቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ፊት ለፊት መድረክ ለቋሚ ኮሚቴ አባላት ያቀረቡ ሲሆን ሪፖርታቸውን ቋሚ ኮሚቴው በዝርዝር በመገምገም ግብረ-መልስ ሰጥቷል። እንዲሁም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ እና የሁሉም ተቋማትን የግማሽ ዓመት ሪፖርት በጥልቀት በመገምገም ግብረ-መልሱ ለየተቋማቱ ተልኳል።

## 4. የአደረጃጀት ዘርፍ ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ

- የቋሚ ኮሚቴው አመራሮችም ይሁን አባላቶች የእርስ በርስ የመደጋገፍ ሁኔታ የሚበረታታ እና ለስራ ያላቸው ተነሳሽነት የሚመሰገን ነው።

## 5. ሌሎች ተግባራት

5.1. የተጠያቂነትን ስርዓት መዘርጋት፣

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

- ተቋማት የተጠያቂነትን ስርዓት መዘርጋታቸውንና ለትግበራም በዕቅዳቸው ማካተታቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

5.2. የሴክተር ዘለል (cross cutting issue) ተግባራት በተገቢ መልክ ታቅዶ እየተፈፀሙ መሆናቸውን መከታተል።

**የተከናወኑ ተግባራት፡-**

- ከሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች፣ ከኤች አይቪ ኤድስ ጋር ያሉ ዜጎች እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን በሚመለከት እንዲሁም የመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት አካባቢ ጥበቃ ስራዎችን አስመልክቶ እየተገበሩ መሆናቸውን እየተከታተልን እንገኛለን።

- **በሪፖርቱ ውስጥ ያልተካተቱ ግቦች በቀጣይ ወራት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው።**

## ማጠቃለያ

ቋሚ ኮሚቴው በ2014 በጀት ዓመት በግማሽ ዓመት ውስጥ በዕቅዱ እና በቼክ ሊስቱ መሰረት ያቀዳቸውን ተግባራት አብዛኛዎቹን መፈፀም መቻሉ እና በተለይ የፌደራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚያስገነባቸው የመንግስት ህንፃ ግንባታ ላይ የከተማ መደበኛ መስክ ምልከታ ተከናውኗል፡፡ በዚሁ ለቀጣይ የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ስራችንን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

## የ2014 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የከተማ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በስብሰባ ቀናት

## <u>የተገኙና ያልተገኙ አባላት ዝርዝር</u>

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | የሥራ ኃላፊነት | መገኘት የሚገባው ቀን ብዛት | የተገኙበት ቀናት | ያልተገኘበት ቀናት | ያልተገኙበት ምክንያት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በሌላ ተልዕኮ | መስክ | በህክምና | ፍቃድ | ወሊድ | ኢክል | ቀሪ | ምርመራ |
| 1. | የተከበሩ ወ/ሮ ሸዊት ሻንካ | የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 2. | የተከበሩ ዶ/ር እሸቱ ተመስገን | የቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 3. | የተከበሩ ወ/ሮ ገነት ከተማ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 4. | የተከበሩ አቶ ፍራኦል ኡዴሳ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 5. | የተከበሩ አቶ ጀማል አልዪ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 6. | የተከበሩ አቶ ተሾመ ዋለ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 7. | የተከበሩ ወ/ሮ ፍቅር አባይ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 8. | የተከበሩ ወ/ሮ ታለፍ ፍታወቅ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 9. | የተከበሩ አቶ ጋሻያለው ጋላ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 10. | የተከበሩ አቶ አዝመራ አንዴሞ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 11. | የተከበሩ አቶ ፍቃዱ ጋውሻሎ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |
| 12. | የተከበሩ አቶ በቀለ ፎሌ | አባል | 2 | 2 | | | | | | | | | |